# ለሞት የቀረበ

## ክፍል ፩

ከበልጅግ አሊ

ክረምት ሊገባ ነው ።ለአረጀው አጥንቴ የአውሮፓ ክረምት እንደማይስማማኝ ስለማውቅ እጠላዋለሁ ። የዛሬው ቀንማ በተለይ በጣም የጨፈገገ ነው ። ያስጠላል ። ልብ ውስጥ ሃዘን ሳይገባ ትካዜን ይፈጥራል ። ከቤቴ መስኮት ላይ ቆሜ ወደ ውጭ ስመለከት ተፈጥሮ ለዚህ ለሚመጣው ለሚያስጠላ ክረምት ውበት እንደሰጠው ተመለከትኩ። ዛፎቹ ሁሉ ቅጠሎቻቸውን በሙሉ አላረገፉም ። አብዛኛዎቹ ወደ ወርቅማነት ለውጠው ለክረምቱ መቀበያ አዲስ ልብስ የለበሱ ይመስላሉ። ሃሳብ ይዞኝ ሄደ። በዚህ ሃዘንን በሚቀሰቅስ የአየር ጠባይ የራሱ የሆነ የሚያስደስት ዐመል መታከሉ ገረመኝ ።በሃዘን ውስጥ የሚገኝ ደስታ እኮ ወደር የለውም ። “የሰው ልጅ ስንት የሃዘን ወቅቶች ያሳልፋል ?“ ብዬ እራሴን ጠየቅሁ። እንደገና ሃሳቤ ወደ ሌላ ቦታ ተበተነ ። የሞት ጥላ ያንዣበበት የሚመስለውን ጥቁር ያለውን ሰማይ ተመለከትኩ ። የዓለም መጨረሻው እንዲህ ይሆን? ዓለም መጨረሻ ይኖራት ይሆን ? ዓለም መጨረሻ ኖራትም አልኖራትም ሞት የሰው ዘር ከዓለም የሚለይበት ነው ። ስለሞት ማሰብ ጀመርኩ ። የአቤልና የቃየል ታሪክ ትዝ አለኝ ። የቃዬል ዕድል ለምን በገዳይነት ተፃፈ ብዬ አሰላሰልኩ ። ጥላቻ ?!--ዕጣ ክፍሉ ?--! ።

ከመስኮቱ አጠገብ ካለው ጠረቤዛ ላይ አንድ ኮምፒውተር አለ ።ተከፍቶአል። ፓልቶክ ይጮኻል ። የአንዲት ሴትዮ ድምፅ አዶከበሬው እንደተነሳበት ወይም አጋንንት ሰፍሮበት ሲቃ እንደያዘው ሰው ታጓራለች።“ኢሕአፓ ይወድማል! ሞት ለኢሕአፓ“ የማትለው የለም ።ከዚህ ቀደም ተመሳሳይ ድምፅ የሰማሁ ይመስለኛል። ምን ሆና እንደሆን ላውቀው አልቻልኩም።ነገር ግን የአጋንንቶች አለቃ ሌጊዮን የሰፈረባት ትመስላለች።የሚያስጓራት ጥላቻ ይሆን ? የቃዬል ዕድል ? ።የሠፈሬ ታቦት ልደታን ምህረቱን እንድትልክላት ተማፀንኩ ። የኮምፒውተሩን ድምፁን ቀንሼ ወደ ውጭ መመልከቴን ቀጠልኩ ።

አሮጊቶች ትልልቅ ካፖርት ለብሰው ያዘግማሉ ። ሕፃናት በበጋው አካባቢውን እንደማይሞሉት አሁን በብርዱ ምክንያት ጠፍተዋል ። የሕፃናቱ ሁኔታ ሁል ጊዜ ይገርመኛል።በክረምት ሰውነታቸው በልብስ ተጠቅልሎ ማንነታቸውን ለማወቅ የሚያስቸግር ይሆናል ።ክረምቱ አልፎ በጋው ሲተካ ቁመታቸው አድጎ ሌላ ልጅ መስለው ብቅ ብቅ ይላሉ ። ሌላ የደስታ ወቅት! በጋው ይጀምራል። ሕፃናት አካባቢውን ይሞሉታል። ከበጋው ጋር አዲስ ተስፋ ብቅ ይላል። የደስተኛ ፊት በየአንዳንዱ ላይ ይነበባል።

ከአፍሪካ ወደ እስያ ፣ ከአውሮፓ ወደ አሜሪካ ሃሳቤ ዝብርቅርቅ ብሎ አንዱን ማንሳት አንዱን መጣል ጀመርኩ ።ሰለ በጋው ሳስብ ያለፈዉ በጋ ሙቀት ታሰበኝ። ይህም በፈንታዉ ስለ እስርቤት ሙቀት አስታወሰኝ ። ከፍተኛ 22 ቀበሌ 07 ውስጥ የነበረው ሶደሬ በመባል የሚታወቀው የእስር ክፍል ፊቴ መጥቶ ድቅን አለ ። እዛች ትንሽ ክፍል ውስጥ የሰው ልጅ እንደ ሰርዲን ተጠቅጥቆ ፣ የራሱ ላቦት እንደዝናብ ሲዘንብበት ፣ የመኖር ተሰፋው ጨልሞ ፣ለሞት የቀረበ ሆኖ ፣ በፍርሃት ጊዜ ብቻ በሚፈጠር የብብት ላብ ሽታ ታፍኖ ፣ በጩካኞች ጠዋት ማት እየተዋረደ ፣ እስትንፋሱ የምትቆምበትን ሰዓት ሲቆጥር የነበረበት ወቅት ታወሰኝ ።

ስለ እስር ቤት ሳወጣና ሳወርድ በግድያ ወንጀል ተፈርዶበት ፣ ሰሜን አሜሪካ ቴክሳስ ውስጥ የሞት ቀኑን በመጠባበቅ ላይ የነበረዉ የደብዳቤ ጓደኛዬ ትዝ አለኝ ። „እንዴት ነበር የተተዋወቅነው ?“ ራሴን ጠየቅሁ ። አምነስቲ ኢንተርናሽናል ውስጥ የምትስራ አንዲት የ75 ዓመት አሮጊት ጠይቃኝ ነበር ግንኙነቱን የጀመርኩት። በደብዳቤ ይህንን ብቸኝነት የሚሰማውን እስረኛ ማፅናናት እችል እንደሆን ተማፀነችኝ። ነፍሰ ገዳይ ፣-- ሞት የተፈረደበት ፣-- ከዚህ በፊት የማላውቀው ፣-- እንዴት ይሆናል ?። ለብዙ ጊዜ ምንም ሳላደርግ ቆይቼ እስቲ ለገና በዓል

እንኳን አደረሰህ ልበለው ብዬ ጀመርኩት ። ስንት ጊዜ አለፈው ባካችሁ ? እኔ ስንት ቦታ ደርሻለሁ? እሱ ግን በዚያች ጠባብ ክፍል ውስጥ ለሞት ቀርቦ ፣ ሞትን እየጠበቀ ነው።

ኮምፒዉተሩ ይጮኻል ። ተናጋሪዋ አሁንም ታጓራለኝ ። ውጩ አሁንም እንደጠቆረ ነው ። በዚህ ሃዘን በሚቀሰቅስ ቀን የሚያስደስት ነገር መስማት ይቻል ይሆን ብዬ ከአንዱ የፓልቶክ ክፍል ወደ ሌላው መዝለል ጀመርኩ ። ወጣቶች ተሰብስበው በብልግና ቃላት የሚሰዳደቡበት የፓልቶክ ክፍል ስገባ ደነገጥኩና ቶሎ ብዬ ወጣሁ ። እዚያ ክፍል ውስጥ ሰው ቢያየኝ ምን ይለኛል ? በሚስጥር ስም ወደ ፓልቶኩ መግባቴ ተረሳኝ። የእኔ የወጣትነት ዘመን እንደገና ትዝ አለኝ ። እነዚህ የአሁኖቹ ወጣቶች ስለሃገራቸው ምንድነው የሚያስቡት ? በብልግና ቃላት መጠቀማቸው የዘመናዊነት ምልክት ይመስላቸው ይሆን ? ወይስ የጭንቀታቸው ማቃለያ ? ወይስ ማንነታቸውን ለማወቅ የሚደርጉት ትግል ? ምን እንደዚህ ተስፋ አስቆረጣቸው ? ግራ የሚያጋባ ነው ። እንዴትስ መመለስ ይቻል ይሆን ? ለጥቂት ደቂቃ አሰብኩበት ፡ ለጥያቄዬ መልስ ባጣለት ወደ ራሴ የወጣትነት ዘመን ውስጥ ገባሁ ።

ይህ የጠቆረ ቀን ሃብተ ጊዮርጊስ ድልድይን እንዳስብ አደረገኝ ። ያ የቆሸሸ ጥቁር ውሃ ፣ ያ የሚገማ ቱቦ ፣ ያ የበረንዳ አዳሪዎች የመፀዳጃ ቦታ ፣--- ያንገፈግፋል ። በደርግ ይደረግ የነበረውን አሰሳ ለመደበቅ ስንል ለሳምንት የአደርንበትን የቆሻሻ ቱቦ እስከ ሕያወቴ ፍፃሜ የምረሳው አይደለም ። የውጪዉ ጥቁረት በዚያ ክፉ ዘመን በፊታችን ላይ ይነበብ የነበረውን ሃዘን ይመስላል። በፓልቶክ ክፍል ውስጥ የሚሰማው „ ሞት ለኢሕአፓ ፣ ሞት ለኢሕአፓ“ የሚለውን መፈክር አስታወሰኝና እንደገና ፊቴን አጠቆረው ። የሠፈሬ አብዮት ጥበቃ አባል የነበረችው ማይም ሴት ይህንን መፈክር ደጋግማ ታሰማ ነበር ። በካቲካላና በምታጨሰው ሲጋራ ፊቷን ያበላሸች ነበረች ። ሰውነቷ ተበልቶ አልቆ፣ ፃዕረ ሞት መስላ ላያት በእራሷ ላይ ያደረገችውን ቅጣት አይስተውም። ሱስ ከሆነባት መጥፎ ጠባይ መላቀቅ አቅቷት ፣ የሴትነት ውበቷ ተሟጦ አልቆ ፡ ችግሯን ማቃለያ ስታጣ፣ ሞት ለኢሕአፓ እያለች መጨፈርን ታዘወትራለች ። በካቲካላ ምትክ የሰው ደም እየታሰባት ይሆን ? በውቅቱ በነበረው ፖለቲካ ጠቃሚ ሰው ተደርጋ ሰለምትቆጠር የምትናገረውን ፣ የምታወርደውን መፈክር ፣ ብዙ ሰው ተሰብስቦ እየሰማ ይታዘባት ነበር ። “ያ ሁሉ ወጣት ለምን ተገደለ ?“ብዬ አሰብኩ ። የአቤል ዕድል ! ጥላቻ ታሰበኝ !

ትንባሆ ሞኖፖል አጠገብ የነበረው ከፍተኛ 22 ቀበሌ 07 ፣ከሰተን ፣ ትንሳኤ ንና፣ ሃይለማርያምን አስታወስኩ ። የስንት ሰው ሕይወት በእጃቸው ይኖር ይሆን ? ለማ ፣ አርጋው ፣ ሻንበል ደስታ ፣ ሌሎችም ። ልደታ ፣ ቢሪሞ ፣ ቶሎሳ ሰፈር ፣ አንበሳ አውቶብስ ፣ ሜክሲኮ ፣ አሁን ምን ይመስሉ ይሆን ? ለመጨረሻ ጊዜ እዚያ የነበርኩት የዛሬ 20 ዓመት መሆኑ ትዝ አለኝ ። ጊዜው እንዴት ይበራል ?/-- 20 ዓመት......

ሰሜን አሜሪካ ቴክሳስ ውስጥ የሞት ፍርዱን ይጠብቅ የነበረው የደብዳቤ ጓደኛዬ በነፍስ ገዳይነት ሲወነጀል የሃያ አመት ልጅ ነበር ። አሁን ቴክሰስ ውስጥ የሚገኘው Polunsky unit በመባል የሚታወቀው የሞት ፍርድ የተፈረደባቸው እስረኞች የሚታሰሩበት እስር ቤት ውስጥ ነው ያለው ።

ሃሳቤ አንድ ቦታ ማረፍ አቃተው፡፡ በጠባቧ ክፍል ውስጥ በአንድ የመፃህፍት መደርደሪያ ላይ ያሉትን መፃህፍት መመልከት ጀመርኩ ። የምፈልገውን መፃህፍ አገኘሁ ፡፤ የፊዮዶር ዶስቶዬቭስኪ ( Crime and Punishment ) ነበር ። አውጥቼ ተመለከትኩት ። ራስኮልኒኮቭ ዋናው ገፀባሕሪ ለምን አራጣ አበዳሪዋንና እህቷን ገደለ ብዬ አስብኩ ። መፀሐፉን ማገላበጥ ጀመርኩ ። ራስኮልኒኮቭ ሁለቱን የገደላቸው ታላቁ ሳይኮሎጂስት ( Sigmund Freund) እንደሚለው ( Übermensch) ከሕግና ከሕብረተሰቡ በላይ መሆን ፈልጎ ነው ። እንደገና አሳቤ ተበተነ ።

ሌላ የፌዶር ዶስቶዮቭስኪ መፀሐፍ ትዝ አለኝ ።በካማራዞቭ ወንድማማቾች (The Brothers Kamarazov) ውስጥ ኢቫን ካራማዞቭ አንዴ እንዲህ ብሎ ነበር ። „ If God does not exist , everything is permitted „ . በቀይ ሽብር የተገደሉት የጆሆቫ ሃይማኖት ተከታዮች ትዝ አሉኝ።

"ሞት ለኢሕአፓ" የሚለውን መፈክር አናሰማም ስላሉ መገደላቸውን አስታወስኩ ። ቀልቤን ሰባስቤ ወደ ሴትየዋ የፓልቶክ ክፍል ወሰድኩት... አሁንም ሞት ለኢሕአፓ ብላ ታጓራለች ። የሰው ደም አይቶ እንደሚደሰት ጂኒ ደግሞ በቀጭን ድምፅ የሚያቃጭል ሳቅ ታሰማለች ።... በዚህ መፈክር የተነሳ ሕይወታቸዉን ያጡት ሃይማኖተኞች ትዝ አሉኝ።

ወደ ቀበሌ 07 እንዴት እንደመጣሁ አስታወስኩ።ከከርቸሌ አሁን በትክክል ባላስታውሰውም 7 ወይም 8 እንሆን ይሆናል አንድ ላይ የመጣነው። ከከርቸሌ እስከ ትንባሆ ሞኖፖል ሩቅ አደለም ። ግን ምን እንደሚገጥመው ለማያውቅ ሰው ጉዞው እንዴት ረጅም ነበር ?? ያ ጉዞ ሌላውን ጉዞ አስታወሰኝ ። የቴክሳሱ የደብዳቤ ጓደኛዬ አንድ ቀን የጻፈልኝ ትዝ አለኝ ። ፊልጌ አወጣሁትና ማንበብ ጀመርኩ ።

" ከእንቅልፌ ከጠዋቱ አራት ሰዓት ላይ ቀሰቀሱኝ ። ሰኞ ዕለት ።ቁርስ በላሁና ራሴን ለትልቁ ጉዞ አዘጋጀሁት ። ገና ሃያ አመቴ ነበር ። በዚህ ዓለም ብዙ ነገር አላየሁም ። ወደፊትም የማየት ዕድል እንደሌለኝ አውቀዋለሁ" ።

"ጉዟችንን ስንጀምር ወንበሩ ላይ ደገፍ ብዬ ተቀምጬ ወደ ውጭ መመልከት ጀመርኩ። በሰማይ ላይ ያሉትን ኮኮቦች ተመለከትኩ። ርቀታቸው ረጅም ወደ ሆነ ሃሳብ ውስጥ ከተተኝ። በዚህ ቀዝቃዛ ጠዋት ሃሳቤ ከራሴ ጋር የተያያዘ ነበር። ምን ይገጥመኝ እንደሆን ማሰላሰል ቀጠልኩ። ሰለሚወስዱኝ እስርቤት የሚያስቅቁ ታሪኮች ሰምቻለሁ ፣በፊልምም ተመልክቻለሁ። ምን እንደሚጠብቀኝ ማሰብ አልቻልኩም። ነፍሰ ገዳዮች ሞት ከተፈረደብን በኋላ የሞት ቅጣቱ እስከሚፈፀምብን ድረስ ሞትን ስለምንጠብቅበት ቦታ አስቃቂነት ከመስማት ብዛት በተፈጠረብኝ ፍርሃት የተነሳ ሰውነቴ ይንቀጠቀጥ ጀመር።"

"ከጠዋቱ ስምንት ሰዓት አካባቢ ሽንትሰቪል ደረስን (Diagnostic Unit in Huntsville). በቀይ ሸክላ የታጠረና የተከበበ እስር ቤት አለፍ አለፍ እያለ በዘበኞች ቤት ታጅቧል። ሁለቱ ጠባቂዎቼ በመኪናው ጀርባ በኩል አወረዱኝና በአጥሩ ውስጥ ከሚገኘው ትልቅ ቤት ውስጥ ይዘውኝ ገቡ።በርካታ በሮችን ካለፍን በኋላ ከአንድ ዐይኖቹ ከሚቅዘበዘበዙ አጭሬ ሃምሳ አለቃ ዘንድ አቀረቡኝ ።"

አምሳ አለቃው ከፊት ለፊት ከሚገኙ አራት ጠባባብ ክፍሎች ውስጥ አስገብቶ ልብሴን በሙሉ እንዳወልቅ አዘዘኝ ። ፍተሻ በሁሉም እስር ቤቶች የሚገኝ የየእለት ተግባር ነውና አልተደነቅሁም ። ነፃነትህን ስታጣ ምንም የግል የሆነ ሚስጥር ሰላማይኖርህ ከፊት ለፊት ከተደረደሩት ፖሊሶች ፊት ራቁቴን ቆምኩ። ፖሊሶቹ የዚህን እስር ቤት ኃይለኝነት፣ ከእነርሱ ፍቃድ ውጭ ወይም ትዕዛዝ አለማክበር ሊያደርስ የሚችለውን ለማሳየት እንደ አውሬ ከአጠገቤ ይንጎማለሉ ጀመር ። እጆችህን አንሳ ፣ ጥፍሮችህን አሳይ ፣ አፍህን ክፈት ፣ ምላስህን አሳይ ፣ አጎንብስ ፣ የሚሉት የፍተሻ ሥርዓቶች የተለመዱም ቢሆኑም ፖሊሶቹ ኃይለኝነታቸውን ለማሳየት በመቆጣትና ለመማታት በመጋበዝ ማስፈራራት የተለመደ ተግባራቸው ነው ።

ከዚህ ፍተሻ በኋላ ወደ ሁለተኛው ክፍል ተዘዋውሬ አዲስ ልብስ ተሰጠኝ። ለበስኩና በእጆቼ ላይ ካቴና ተደረገልኝ ። የሃምሳ አለቃው እንድከተለው አዘዘኝና አንድ በመደዳዉ የገላ መታጠቢያ ያለበት ክፍል ገባሁ ። እዚያ ክፍል ውስጥ አንድ ጥልቢያኮስ፣ እስር ቤት ዉስጥ ለዘላለም የኖረ የሚመስል አንድ ሽማግሌ በጥቂት ደቂቃ ዉስጥ ፀጉሬን ከሰውነቴ ሸልቶ አወረደው ።

በፖሊሶች ታጅቤ ወደ አንድ እስረኞች ወደ ተሰበሰቡበት አዳራሽ ገባሁ ። አምሳ አለቃው ሁላችሁም ወደ ግድግዳ ዙሩ ! ብሎ ሲጮህ በአንድ ጊዜ ተሰሚነት አገኘ። ሁሉም እስረኞች ወደ ግድግዳ ዞሩ ። አንድንዶቹ ግን <<ነፍሰ ገዳይ>> << የሞት ፍርደኛ >> ብለው ማንሾካሾክ ጀመሩ ። ቀስ ብለው እያሾለኩ የሚያዩ እስረኞች << ገና ወጣት እኮ ነው >> ሲሉ ይሰማኛል ። ከዚህ አዳራሽ እንደወጣን አንድ መኪና አጠገብ ደረስን።እኔን ለማጀብ የመጡት ፖሊሶች አንዱ ጠይም መልክ ያለውና ብሬድፎርድ የሚባልና ብጭጭ ያለ መልክ ያለት

ቶምሶን የምትባል የሴት ፖሊስ ናቸው ፡፡እንደገና እግሬ ከታሰረ በኋላ ለነፍስ ገዳዮችን ለማጓጓዝ ተብሎ በተሰራ መኪና ብቻዬን እንደ ዱር አዉሬ መሃል ላይ በተሰራ አግዳሚ ወንበር ላይ ተቀምጬ፣ የተባይ መከላከያ መድሃኒት የሚመስል ነገር እየሸተተኝ ወደ << ELLIS UNIT >> ተወሰድኩ ፡፡ እስር ቤቱ ከሌሎቹም የተለየ ባይሆንም አንድ የሚያስፈራራ ስሜት እየተሰማኝ መጣ፡፡ ብሬድፎርድ እየረዳኝ ከመኪናው ከወረድኩ በኋላ እንድንበረከክ ታዘዝኩ ፡፡ከዛም እግሬ ላይ የታሰረው ተፈታልኝ፡፡ ጣራው ላይ ቆሞ ጠመንጃዉን ወደ እኔ ያነጣጠረዉን ፖሊስ እየተመለከትኩ የማደርገው ጨንቆኝ እጠብቅ ጀመር ፡፡ ቶምሶን እዘው ተንበርክከህ ልትቀር ነው እንዴ? አትነሳም ወይ? ብላ ስታንባርቅብኝ ተውተርትሬ ተነሳሁና እነርሱን መከተል ጀመርኩ ፡፡

አንድ ትልቅ በር ተከፈቶልን ስንገባ ሙቀት ያለው አየር ተቀበለን ፡፡ ጠበብ ባለ መንገድ ወደ ፊት ተጓዝን በቀኝ በኩል 20 የሚሆን ሽንት ቤት ተደርድሯል ፡፡ በስተግራ ደግሞ የመታጠብያ ቤቶች አሉ ፡፡ ትንሽ ወደ ፊት ስንሄድ በግራና በቀኝ ግማሽ ማይል የሚሆን እስረኞች የታጎሩባቸዉ የእስር ክፍሎች ተደርድረዋል ፡፡ እንዳለፈው እስር ቤት እዚህኛው በመምጣቴ የተደነቀ አልነበረም ፡፡ ሶስት አራተኛውን መንገድ እንደተጓዝን በሰማያዊ ቀለም ከተከለለ አንድ ክልል ደረስን ፡፡ ይህ ሞት የተፈረደብንን እስረኞች ከሌሎቹ ወንጀለኞች የሚለያየን መሆኑን ተረዳሁ ፡፡ ቀና ብዬ ስመለከት በእንጨት የተፃፈ ጽሁፍ ይነበባል

<< WELCOME TO TEXAS DEATHROW - WELCOME>>

ደብዳቤውን አጣጥፌ አስቀመጥኩና ወደ ሃሳቤ ተመልሼ ገባሁ ፡፡ከከርቸሌ ወደ ቀበሌ 07 በተወሰድን ጊዜ የነበረው ሁኔታ ትዝ አለኝ ፡፡ አለም በቃኝ በራፍ ላይ እጃችን ታስሮ በመኪና ታጭቀን ወደ ትንቧሆ ሞኖፖል ተወሰድን፡፡ ትንሽ ከተጓዝን በኋላ አንዲት ጠባብ መንገድ ላይ ታጥፈን ስንሄድ ልጆቻቸዉ የታሰሩባቸዉ ብዙ እናቶችና አባቶች ድንጋይ ላይ ተኮልኩለው ተቀምጠዋል ፡፡ እኛ ስንገባ እነማን እንደሆንን ለማወቅ ወደ መኪናው ሲጠጉ አብዮት ጥበቃዎቹ ጠበንጃዎቻቸውን እያቀባበሉ አባረሯቸው ፡፡ ወደ ውስጥ ስንገባ በራፉ ላይ በትልቁ አንድ መፈክር ተሰቅሏል፡፡

<< ከፍተኛ 22 ቀበሌ 07 - ቀይ ሽብር ይፋፋም >>

.............................................***..........................................

ይቀጥላል

ሰለኛ የሚያስብ በሰላም ይክረም

ይህንን ፅሁፍ በሚመለከት ሀሳብ መስጠት ለምትፈልጉ በዚህ ኢሜል አድራሻ ተጠቀሙ፡፡
beljig.ali@gmail.com

Ethio Lion .Com